# ኢትዮጵያ፡ለዘላለም፡ትኑር!!!።

ገጽ፡፩-፲፩፤

ማክሰኞ፤መስከረም፡፪፡ቀን፡፪ሺ፬፡ዓመተ፡ምሕረት፤
Tuesday, September 13, 2011 A.D.




መይሣው፡ካሣ፡ዳግማዊ፡ዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ያስተማሩት፡ጀግንነትን፤አንድነትንና፡የኢዮጵያን፡ግዛት፡ወደ፡ነበረችበት፡ለመመለስ፤ከሕንድ፡ውቅያኖስ፡እስተ፡ማደጋስካር፡ለማስፋት፡መጣርን፡ነበረ፡እንጂ፡ወደ፡ጎጠኝነት፡ለመመለስ፡አልነበረም።ስለዚህ፤እምዬ፡ዳግማዊ፡ዐፄ፡ምኒልክና፡ወሬሣው፡በዝብዝ፡ካሣ፡ዐፄ፡ዮሐንስን፡ካስተማሯቸው፡በኋላ፤እምዬ፡ዳግማዊ፡ዐፄ፡ምኒልክ፡በተማሩበት፡ሲጠቀሙ፡ዐፄ፡ዮሐንስ፡ግን፡የዐፄ፡ቴዎድሮስን፡የቆራጥ፡አመራርን፡አድራጎት፡በሚገባ፡ቢያውቁም፤በስሜኑ፡ተወስነው፡ከበጌምድር፤ጐጃምና፡ወሎን፡በመዝረፍ፤እጅና፡እግር፡በመቁረጥ፡ከማሰቃየት፡አልተቆጠቡም።

ዐፄ፡ዮሐንስ፡፬ኛ፡ለዐፄ፡ቴዎድሮስ፡አሽከርነት፡ገብተው፡ይተደደሩ፡ስለ፡ነበረ፤ልክ፡እንደ፡ጌታቸው፡ዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ተመሳሳይ፡ዓላማና፡ምኞት፡ሲሆን፤የሀገር፡ውስጥ፡አስተዳደርን፡አስመልክቶ፡በአፈጻጸም፡ላይ፡እጅግ፡በጣም፡ይለያያሉ።ከልዩነታቸውም፡አንዱና፡ዋናው፤የክርስቲያን፡ተዋኅዶ፡ሃይማኖት፡አክራሪነታቸው፡ነበረ።ዐፄ፡ዮሐንስ፡የአንድ፡አገር፡ሕዝብና፡ጥንካሬው፡መለኪያ፡ሚዛኑ፡በቋንቋ፤በሃይማኖትና፡በዓላማ፡አንድ፡ሲሆን፡ብቻ፡ነው።በማለት፡ኢትዮጵያዊው፡ሁሉ፡ኦርቶዶክሳዊ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ተከታይ፡እንዲሆን።የሚናገረው፡ቋንቋም፡አማርኛ፤የሀገሪቱ፡ሰንደቅ፡ዓላማ፡በአረንጓዴ፤ቢጫና፡ቀይ፡እንዲዉለበለብ።የሚል፡ሲሆን፡-ዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ግን፡ሃይማኖትን፡አስመልክቶ፡ማንኛውም፡ኢትዮጵያዊ፡የግል፡መንፈሳዊ፡እምነቱን፡እንደ፡ያዘ፡የአንዱ፡እምነት፡የሌላውን፡ሳይነካ፡ሁሉም፡በእኩልነት፡የሀገራቸውን፡መብትና፡ግዴታ፡ማስከበርና፡መወጣት፡አለባቸው።ይህንም፡በትክክል፡መፈጸሙን፡መንግሥት፡ክትትል፡ማድረግ፡አለበት፡የሚል፡ነበረ።

"ዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ምንም፡የግል፡እምነታቸው፡ጠንካራ፡የኦርቶክስ፡ተዋኅዶ፡መሆኑ፡ባይካድም፤ከኦርቶክስ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ባለ፡ሥልጣኖች፡ጋር፡የነበራቸው፡አለ፡መግባባት፡ያስከተለውን፡መዘዝ፡ያውቁ፡ስለ፡ነበረ፤ዐፄ፡ዮሐንስ፡አዲሱን፡መንግሥታዊ፡መመሪያቸውን፡ሲቀይሱ፡-የሀገሪቱ፡ብዙኀኑ፡ምሁራንም፡የቤተ፡ክህነት፡ሰዎች፡ስለ፡ነበሩ፤ከነሱ፡ጋር፡ላለ፡መጋጨት፡በጣም፡ይጠነቀቁ፡ነበር።በቤተ፡ክህነት፡ድጋፍም፡በጣም፡ይተማመኑ፡ነበር።"*፩፤ገጽ፡፳፪፡ኢትዮጵያ፡፲፰፻፵፯-፲፱፻፳፯፡ዓመተ፡ምሕረት።በሜጀር፡ጄኔራል፡ነጋ፡ተገኝ።

ዳግማዊ፡ዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ከቤተ፡ክህነት፡ሰዎችና፡እንግሊዝ፡ጋራ፡የተጣሉበት፡ምክንያት፡የኢትዮጵያን፡አንድነትና፡ልማት፡ለመመሥረት፡ካላቸው፡ሐሣብ፡ጋራ፡አብረው፡ሊራመዱ፡ባለ፡መቻላቸው፡ነበረ።እንግሊዝ፡መንግሥትን፡-"ባገሬ፡ውስጥ፡መድፍና፡ጠመንጃ፡የሚሠራበት፡ቤት፡ለማቋቋም፡በጋፋት፡ዠምሪያለሁና፡የዚህን፡ሥራ፡የሚያውቁ፡በርካታ፡ሰዎች፡ከነ፡መሣሪያቸው፡ካላከልኝ"፤

ካህናቱን፡-

"ይህ፡አርግራጊ፡(አረግራጊ)፤
አቴና፡ወጊ፤
ራሱን፡ታጣቂ፤

ወገቡን፡ሰባቂ፤

እያሉ፡ይዘልፉት፡ዠመር፡(ጀመር)።*፪፡ገጽ፡፳፯፤ቅንፎች፡ከእኛ፡ናቸው።*፪፤-የኢትዮጵያ፡ታሪክ፤ከዐፄ፡ቴዎድሮስ፡እስከ፡ቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ።በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ።

ለብስጭታቸውም፡መነሻ፡የሆነባቸው፡-“በትግሬ፡በዝብዝ፡ካሳ፡(ዐፄ፡ዮሐንስ)፤በላስታ፡ዋግ፡ሥዩም፡ጐበዜ፡(ዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ)፤በሸዋ፤ከመቅደላ፡ያመለጡት፡ምኒልክ፡(ዐፄ)፡ሌሎችም፡ሹማምቶች፡በዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ላይ፡ተነሡባቸው።ለዚሁም፡የሚወዷቸው፡ባለቤታቸው፡እቴጌ፡ምንትዋብ፡ሞተው፡ስለ፡ነበረ፡የሚጽናኑበት፡ጠፋ።ከዚያ፡ጊዜ፡አንሥቶ፡(ካ፲፰፻፶፯-፰)፡ከብስጭት፡የተነሣ፡......፡ከጳጳሱም፤ከካህናትም፤ከመኳንንቱም፤ከተራው፡ሕዝብም፤ከነጮም፡ጠበኛ፡ሆኑ።በፊታቸው፡በታማኝነት፡የሚገመት፡ጠፋ”።*፫፡ገጽ፡፳፯፤-የኢትዮጵያ፡ታርክ፤ከዐፄ፡ተዎድሮስ፡እስከ፡ቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ።በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ።

ዐፄ፡ዮሐንስ፡ከዐፄ፡ቴዎድሮስ፡የወረሱት፡አጨካከናቸውን፡ስንገመግምም፡የኦርቶዶክስ፡ሃይማኖት፡አክራሪነታቸው፡የሥልጣን፡ጥማቸውን፡ለማርካት፡እንጂ፡አድራጐታቸው፡ሃይማኖተኛ፡ንጉሥ፡የሚሠራው፡መስሎ፡አልታዬንም።

ዐፄ፡ዮሐንስ፡፬ኛ፡አማርኛና፡ትግርኛ፡ተናጋሪውን፡ሕዝብ፡እንዴት፡አድርገው፡እንዳስተባበሩት፡ለሠራዊታቸው፡ይሰጡት፡የነበረው፡የማያቋርጥ፡ምክር፡-“ኢትዮጵያዊነት፡ከክብር፡ሁሉ፡በላይ፡ስለ፡መሆኑ፤ይህም፡ክብር፡የተገኘው፡በአባቶቻችን፡አገር፡ወዳድነት፤በነፃነት፡መኩራት፤እንግዳ፡ተቀባይነት፤ቅን፡አስተናጋጅነት፤እነዚህን፡ሁሉ፡በምንም፡ዓይነት፡መለወጥ፡የማይገባቸው፡ስለ፡መሆናቸው፡ነበር”* *፬፤ገጽ፡፳፬፤-ኢትዮጵያ፡፲፰፻፶፯-፲፱፻፰፯፡ዓመተ፡ምሕረት።በሜጀር፡ጄኔራል፡ነጋ፡ተገኝ።

ደግሞም፤“..........መኳንንቶቻቸው፡ወደ፡ንጉሠ፡ነገሥቱ፡ገብተው፡“ጃንሆይ፡ሁላችንም፡እስከ፡ምጥዋ፡ወርደን፡ኢጣሊያኖችን፡ከእናታችን፡ከኢትዮጵያ፡ምድር፡እናስወጣቸው፡ይፍቀዱልን፡አሏቸው”።እርሳቸውም፡በመኳንንቱ፡አነጋገር፡ተደስተው፡.........፡መኳንንቶቼ፤ልጆቼና፡ሕዝቦቼ፡ሆይ!፡እኔም፡ስለ፡እናቴ፡ኢትዮጵያ፡ሕይወቴን፡ልሠዋላት፡ሙሉ፡ፈቃድ፡አለኝ።በኔ፡ልብ፡ያለው፡በናንተ፡ልብ፡ስለ፡መታሰቡ፡በጣም፡ደስ፡ብሎኛል።እንግዲህ፡አሳባችን፡አንድ፡አሳብ፡ከሆነ፡ጠንክሩ፡እንጂ፡አትፍሩ።ለዘመቻውም፡አሁን፡አዋጅ፡እነግራለሁና፡አይዟችሁ፡በርቱ።.........”፡ቀጥለውም፡-“የኢትዮጵያ፡ልጅ፡ሆይ!፤ልብ፡አድርገህ፡ተመልከት።ኢትዮጵያ፡የተባለችው፡አንደኛ፡እናትህ፡ናት።ሁለተኛ፡ዘውድህ፡ናት።ሦስተኛም፡ሚስትህ፡ናት።ዐራተኛም፡ልጅህ፡ናት።አምስተኛም፤መቃብርህ፡ናት።እንግዲህ፤የእናት፡ፍቅር።የዘውድ፡ክብር።የሚስት፡ደግነት።የልጅ።ደስታ።የመቃብር፡ካባቲነት፡(ታቃፊነት)፡እንደዚህ፡መሆኑን፡ዐውቀህ፡ተነሣ።”*፭፤-አቶ፡ዐጥሜ፤የጋላ፡ታሪክ፤(የእጅ፡ጽሑፍ)፡ ገጽ፡፻፰፫-፻፰፬።-ብላቴን፡ጌታ፡ኅሩይ፡(የእጅ፡ጽሑፍ)፡ገጽ፡፻፴፱።-ዓፄ፡ዮሐንስ፡በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ፡፲፱፻፹፪፤ገጽ፡፴፻፫-፬።

ዘውዱ፡ስለ፡ቀረ፡ሌሎችን፡አሁንም፡ልንጠቀምባቸው፡ይገባል።

አንገራጋሪ፡ፉከራቸውም፡-

“እርሳሱ፡ብዙ፡የሐምሌ፡ቴግብ(ተግብ)፤

ድንጋይ፡መንከስ፡ነው፡ካሴን፡ማሰብ።

ዐፄ፡ዮሐንስን፡ልውጋ፡ብሎ፡መከጀል፡ከንቱ፡ነው።ካሴ፤የካሣ፡(የቀድሞ፡ስማቸው)፡ቁልምጫ፡ነው።”

እርሳሱ፡ብዙ፡ያሉት፡ደግሞ፡ለዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ጥቃት፡ኢጋዥነታቸው፡ከእንግሊዝ፡የተረጠቡትን፡መሣሪያ፡ብዛት፡ነው።እጅግ፡በጣም፡የሚያሳዝነን፡ለከሃዲ፡ውሸት፡ለፍላፊው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ተቃውሞ፡መልስ፡በተቃውሞ፡መስጠታችን፡ነው።“ዝኆኖች፡ሲራገጡ፡ሣሩ፡ይበደላል።”እንደሚሉት፤ስለ፡ዐፄ፡ዮሐንስ፡ማለት፡የማንፈልገውን፡ማስረጃ፡ለማውጣት፡ብለን፡ለመዘክዘክ፡መገደዳችን፡ነው።በዚያን፡ዘመን፡የጥቁር፡ሕዝብን፡መኖሪያ፡አፍርካን፡ቅኝ፡ግዛት፡ለማድረግ፡የውጭ፡አገር፡መንግሥታት፡መቀራመት፡የጀመሩበት፡ስለ፡ነበረና፡በብቸኛዋ፡ኢትዮጵያም፡ውስጥ፡የነበሩ፡ንጉሦች፡እኔ፡እጠቀልል፤እኔ፡እጠቀልል፡በመባባል፡ፉክክር፡ላይ፡ነበሩ።ያ፡በመሆኑ፡የተሻለ፡መሣሪያ፡ለማግኘት፡ፈልገው፡ዐፄ፡ዮሐንስ፡ከእንግሊዝ፡ጋራ፡ወግነው፡የዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ዘመን፡መፈጸሚያ፡ሆነ።

በዐፄ፡ቴዎድሮስ፡ላይም፡ካስጨከናቸው፡አንዱ፡-“ለወንድሞቻቸው፡ለጉግሣና፡ማሩ፡የደጃዝማችነት፡ማዕርግ፡ሲሰጣቸው፡ለርሳቸው፡የባላምባራስነት፡ደረጃ፡ተሰጣቸው።“ካሳ፡በጐልማሳነታቸው፡

ገጽ:፫-፲፩፤
(፲፰፻፶፯-፺:ዓ.ም.):ላፄ:ቴወድሮስ:አሽከርነት:ስለገቡ፤ለወንድሞቻቸው:ለጉግሣና:ለማሩ:የደጃዝማችነት:ማዕረግ:ሲሰጣቸው:ለእርሳቸው:የባላምባራስነት:ደረጃ:ተሰጣቸው።ይኸም:በ፴፫:ዓመት:ዕድሜያቸው:አካባቢ:መሆኑ:ነው።ታላላቆቻቸው:ቢሆኑም:ወንድሞቻቸው:የደጃዝማችነት:ማዕረግ:ሲያገኙ:ከእርሳቸው:በዕድሜ:፲፩:ዓመት:የሚያንሱት:የሸዋው:መስፍን:ምኒልክ:በአማችነት:ደጃዝማች:ሲባሉ:የእርሳቸው:ባላምባራስነት:ሳያሳዝናቸው:አልቀረም።ያሸፈታቸውም:ምክንያት:ይኸው:ነው:ይባላል።በሸፈቱበት:ጊዜ:ካፄ:ቴዎድሮስ:ለትግራይ:ግዛት:የሚላኩትን:ጉልበት:ሲሰማቸው:እዬ:ተዋጉ፣ዐቅም:ሲያንሳቸው:ወደ:ደንከል:በረሃ:እዬ:ሸሹ:ከባላባቱ:ጋር:በመተባበር:ኑረዋል።በዚያን:ጊዜ:ነው:ከባላባቱ:ልጅ:ከደንከሊቱ:ተወላጅ:ጋር:ተጋብተው:አርኣያን:የወለዱ።"*፰፤-ዐፄ:ዮሐንስ:ገጽ:፵፭-፪:በተክለ:ጻድቅ:መኩሪያ።፲፱፻፹፪፤ዓ.ም.

## የትግራይ:ሥልጣን:ጥመኞች:አባትና:የልጅ:ልጅ፤


ዓፄ:ዮሐንስ:፬ኛ።

ኤርትራዊው:ዓረብ:አረመኔ:አመፀኛው:ለገሠ:ዜናዊ:አሥረሥ:ስድብና:የአነጋገር:ብልግናን:የተማረው:ከዓፄ:ዮሐንስም:ለመሆኑ:ዛሬ:በትንሹ:ለመጻፍ:ያነሣሣን:በፊት:ገጹ:የዓፄ:ቴዎድሮስንና:ዓፄ:ምኒልክ:ንግግሩ:በሰጠነው:አስተያየት:በለገሠ:ሳንባ:የሚተነፍሱ:የትግራይ:አመፀኛ:ወያኔዎች:እዬ:ተሳደቡ:ስላስቸገሩን፤ትምህርት:ልንሰጣቸው:ፈልገን:ነው።ኢትዮጵያችንን:አብረን:እንኑርባት:ስንል:ይዋጥላቸዋል:በሚል:ግምት:ግን:አይደለም።

ዓፄ:ዮሐንስ:፬ኛ፣በታሪካቸው:ለኢትዮጵያ:አንድነትና:ለተዋኅዶ:ሃይማኖት:ቀናተኛ:እንደ:ነበሩ:ይነገራል።አባባሉ:ተገባራዊና:መንፈሳዊ:መስሎ:ስላልታዬን:የአስተዳደር:ጥንካሬያቸውንና:ድክመታቸውን:ሕዝብ:እንዲ:መረምረው:ለማድረግ:እንሆ!:በማስረጃ:አቅርባናል።እንደኛ:ምርምር:ተንኮለኞች፣ንግግረ:ብልሹዎች፣ባለጌዎች፣ጨካኞች፣ትግራይና:ኤርትራዊ:ዓረብ:የሥልጣን:ጥመኞች:ለኢትዮጵያ:ሕዝብ:ኅልውናና:አገራዊ:አንድነት:ጠንቆች:ናቸው።

"ግዛታቸው:በጠቅላላው:የትውልድ:አገራቸው:ተምቤንና:እንደርታ:በመሆኑ:ይነስ:ይብዛ:አካባቢውን:ሁሉ:ደምስሰው:የትግራይና:ትግሬን:የበላይ:ገዥ:በመሆን:ባላንጣቸው:ተክለ:ጊዮርጊስ:በምጥዋ:በኩል:ጳጳስ:እንዳያስመጡ:እዬ:ተከላከሉ:ራሳቸው:ግን:በ፲፰፻፷፩:ዓ.ም.በአብድራሂም:አለቃ:ብሩና:በመሐመድ:መሪነት:ለግብጽ:ገዥ:ለከዲቭ:ኢስማኤልና:ለፓትሪያርኩ:ለአባ:ድሜጥሮስ:፳ሺ:የማሪያትሬዛ:ብር:ገጸ:በረከት:ልከው:አቡነ:አትናቴዎስን:አስመጥተው:በአጠገባቸው:አስቀምጠው:የንግሣቸውን:ቀን:ሲጠባበቁ:ቆዩ።*፱፤ገጽ:፵፫--ዓፄ:ዮሐንስ፤በተክለ:ጻድቅ:መኩሪያ>፲፱፻፷፪:ዓ.ም.

"ዐፄ:ቴዎድሮስ:ካረፉ:በኋላ:ከዐፄ:ቴዎድሮስ:አሽከሮች:ከራስ:ባሪያው፣ከደጃዝማች:ተክለ:ጊዮርጊስ፣ከደጃች:ሣህሉ:ጋራ:ተዋግተው:ድል:ስላደረጉ፤ከእንግዴህ:ወዲያ:ደጃዝማች:ካሳ:እያላችሁ:ጥሩኝ:ብለው:በፈቃዳቸው:ደጃዝማች:ተብለው:በተንቤንና:በእንደርታ:ገዥ:ሆኑ።ማኅተማቸውም:"ደጃዝማች:ካሳ:ርዕሰ:መኳንንት:ዘኢትዮጵያ":የሚል:ነበር።እንግሊዞች:ዐፄ:ቴዎድሮስን:ለመውጋት:በመጡ:ጊዜ:ላገሩ:እንግዳ:በመሆናቸው:በጣም:ተቸግረው:ነበር።በኋላ:ግን:የትግሬ:ሕዝብ:በደጃች:በዝብዝ:ካሳ:ትእዛዝ:መውጫ:መግቢያውን:እያሳዩ:በራሱ:አገር:አሳልፎ:በውጊያው:ጊዜ:በጦርነት:ስለ:ረዳ:የእንግሊዝ:የጦር:ሠራዊት:አዛዥ:በጣም:ደስ:ብሎት:ነበርና፤ዐፄ:ቴዎድሮስን:ድል:አድርጎ:በሚመለስበት:ጊዜ:ለዐፄ:ተክለ:ጊዮርጊስ:መንግሥቱንና:መሣሪያውን:ይምጡና:ይረከቡ:ቢላቸው:እንቢ:ካሉት:በኋላ:የሁለት:ሬጂመንት:(ክፍለ:ጦር):(የቅንፉ:ከኛ:ነው):ወታደር:የጦር:መሣሪያ:ዐሥራ:ሁለት:መድፍ፣ዘጠኝ:መቶ:ጠመንጃ፣ከዚህም:በቀር:በመጋዘን:አስቀምጦት:የነበረውን:ከልክ:ያለፈ:ጥይትና:ሥንቅ:ለደጃች:በዝብዝ:ካሳ:አስረከባቸው።ደጃች:በዝብዝ:ካሳም:ይህን:መሣሪያ:ቀደም:በነበራቸው:ላይ:አግኝተው:ወታደራቸውን:ውስጥ:ውስጡን:አዘጋጅተው:ከጨረሱ:በኋላ:ለእህታቸው:ባለቤት:ለዐፄ:ተክለ:ጊዮርጊስ:እስከ:ዕድሜ:ልክ:ድረስ:እገዛልዎታለሁ:ብለው:የነበረውን:ቃል:ለውጠው:እንደ:ገና:ለርስዎ:አልታዘዝም:ብለው:ላኩባቸው።

በዚያ፡ጊዜ፡ዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ወሎን፡ለማስገበር፡እስከ፡ዘቢጥ፡ድረስ፡መጥተው፡ነበርና፤የትግሬን፡መሸፈት፡በሰሙ፡ጊዜ፡ሁሉንም፡ትተው፡ወደ፡ትግሬ፡አቀኑ።ወዲያው፡በዛቻ፡ነገሩ፡የሚከናወን፡መስሏቸው፡የወታደራቸውን፡ብዛት፡ለማስረዳት፡አንድ፡ስልቻ፡ጤፍ፡አድርገው፡ወታደሬ፡በዚህ፡ልክ፡ነው፡ሲሉ፡ላኩላቸው።ደጃች፡ካሳም፡የዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡አባት፡አንካሳ፡ስለ፡ነበሩ፡-

ከቱርክ፡ይዋጋል፡እንኳን፡ካንካሳ፣

ያባ፡ፈንቅል፡ልጅ፡ወሬሳው፡ካሳ።

ብለው፡ፎክረው፡ወዲያውኑም፡ወታደርህ፡እንደዚህ፡ቢበዛ፡በጥይት፡ቆልቼ፡ነው፡የምሰደው፡ሲሉ፡ጤፉን፡ቆልተው፡መልሰው፡ላኩላቸው፡ይባላል”።

ዛቻ፡ከተመላለሱ፡በኋላ፡ጦርነት፡ገጥመው፡ዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ተማረኩ።“…………፡ዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስን፡ማረኳቸው፡ወዲያው፡ዓይናቸውን፡በጭካኔ፡አሳውረው፡አባ፡ሰላማ፡በሚባለው፡ተራራ፡አስረዋቸው፡ጥቂት፡ዘመን፡እንደ፡ኖሩ፡ሞቱ።*፱፡ገጽ፡፵፩-፫፤--የኢትዮጵያ፡ታሪክ፡ ከዐፄ፡ቴዎድሮስ፡እስከ፡ቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ።በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ፤፲፱፻፷፪፡ዓ.ም.

“የለመደች፡ጦጣ፡ሁል፤ግዜ፡ሽምጣጣ”።እንደሚሉት፡ከዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ጋራ፡እንደ፡ተለዋወጡት፡ዛቻ፡መስሏቸው፡ለደርቡሽ፡መሪ፡አስቀድመው፡መጣሁ፡ብህ፡ብለው፡በደብዳቤ፡ማስታውቃቸው፡እንደ፡መጣላቸው፡ተናጋሪ፡እንጂ፡እንደ፡ደጃዝማች፡ምኒልክ፡ወይም፡ንጉሥ፡አርቆ፡አሣቢ፡አለመሆናቸውን፡ያሳያል።ከአብሮ፡አደግ፡ጋራ፡ግጭትና፡የውጭ፡አገር፡ጠባዩን፡ከማያውቁት፡ጠላት፡ጋራ፡ምቹ፡ቦታ፡ከያዙ፡በኋላ፡አዘንግቶ፡ይዋጓል፡እንጂ፡እንደ፡ልጅ፡ጨዋታ፡አስቀድመው፡ማንገራገሪያ፡መላክ፡አልነበረባቸውም።የዐፄ፤ተክለ፡ጊዮርጊስ፡ጤፍ፡አላላክም፡ለማዘናጊያ፡የታቀደ፡ነበረ፡እንጂ፡ቢያሸንፈኝም፡በምንም፡መልኩ፡አምቻየ፡ባላምባራስ፡በዝብዝ፡ካሣ፡ምርጫ፡ወይም፡ወሬሳው፡በዝብዝ፡ካሣ፡ምርጫ፡ጨክኖ፡ዓይኔን፡አውጥቶ፡ያሳውረኛል፡ብለው፡የተጠራጠሩ፡አይመስለንም።

ዘዴ፡አልባ፡በኢትዮጵያዊነት፡የወንድ፡ጀግንነት፡ወኔ፡ብቻ፡-“መጣሁ፡ታጠቅ፡እንደ፡ሌባ፡በድንገት፡መጣብኝ፡እንዳትለኝ።መምጣቴም፡የክርስቲያንን፡ደም፡ለመበቀል፡ነው።……………የደርቡሹ፡መሪ፡ከሊፋ፡አብዱላሂ፡ዘኪ፡ቱማልን፡የጦር፡መሪ፡ልኮ፡በጦር፡ግንባር፡አለመኖሩን፡እያወቁ፡ራሳቸው፡በመዝመት፡ፊንታ፡ራስ፡አሉላም፡ቢቀሩ፡በራስ፡ቢቶደድ፡ኃይለ፡ማርያም፡ወይም፡በትልቁ፡ራስ፡አርኣያ፡መሪነት፡በቂ፡ጦር፡ልከው፡እርሳቸው፡ደብረ፡ታቦር፡ወይም፡ጎደር፡ላይ፡ሆነው፡ለማዋጋት፡ቢችሉ፡የተላከው፡ጦር፡እንኳን፡ቢሸነፍ፡እርሳቸው፡አዲስ፡ያልተዋጋ፡ጦር፡ይዘው፡እንደ፡ገና፡ለመሄድ፡በቻሉ፡ነበር”።**፲፤ ገጽ፡፭፻፵፩-፫፡-ዐፄ፡ዮሐንስ።በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ፤፲፱፻፹፪፡ዓ.ም.

በዘመኑ፡ወታደራቸውን፡የሚያስተዳድሩት፡በዝርፊያ፡ስለ፡ነበረ፡የቀላቢነት፡ገፈታ፡ቀማሹ፡አራሹ፡ገበሬ፡ነበረ።እንደ፡ሁኔታው፡ወታደሩ፡በዬቤቱ፡እዬተመራ፡አማርጦ፡ማሩን፣ቅቤውን፣ጠላውን፣ወተቱን፣እርጎውን፡……….ወዘተ፡ይኸን፡አቅርቡ፡እያለ፡እያመናጨቀ፡ሲመገብ፡ያድራል።አንዳንዱ፡ግፍ፡አይፈሬ፡ጥጋበኛ፡ደግሞ፡የገበሬውን፡ሚስቶች፡አስገድዶ፡ሲያደርግ፡ያድራል።በዚህ፡አኳኋን፡የቤገምድር፣የወሎና፡ጐጃምን፡ሕዝብ፡እጅግ፡በጣም፡ስለ፡ጐዱት፡በመማረር፡ይረግማቸው፡ነበረ።“የዐፄ፡ዮሐንስን፡የሠራዊት፡መንጋ፡ለመከላከል፡ንጉሥ፡ተክለ፡ሃይማኖት፡ሙተራ፡መሽገው፡ነበረ።በሌሊት፡ለመያዝ፡የተላከው፡የዐፄ፡ዮሐንስ፡ሠራዊትን፡የአንባው፡ጠባቂዎች፡በናዳ፡ኃይል፡መከላከላቸውንና፡ናዳው፡ሠራዊቱ፡ላይ፡ያደረሰው፡ጉዳት፡አለቃ፡ተክለ፡ሥላሴ፡ዋቅ፡ጅራ፡“ብዙ፡የትግሬ፡ሠራዊት፡ፈጁ”።በማለት፡ያሰፈሩት፡የምስክርነት፡ቃል፡የዐፄ፡ዮሐንስ፡ሠራዊት፡ከአንድ፡ክልል፡የወጣ፡መሆኑን፡ያሳያል።ዐፄ፡ዮሐንስ፡ራሳቸው፡በጐጃም፡ሕዝብ፡ላይ፡የፈጸሙትን፡ከፍተኛ፡እልቂትና፡ዘረፋ፡መደበቅ፡አልቻሉም።“…….በእኔም፡በድሃውም፡ኃጢአት፡እንደ፡ሆነ፡አይታወቅም፡አገሩን፡(ጐጃምን)፡ሳጠፋው፡ከረምሁ፡* …” *፲፩፡ገጽ፡፻፴፯፡ሥልጣን፡ተሻሚ፡ትግሬዎችና፡የኢትዮጵያ፡አንድነት፤፪ሺ፡ዓመተ፡ምሕረት።በተክሌ፡የሻው።

አሁንም፡የትግራይ፡አረመኔ፡ወያኔዎች፡የዐፄ፡ዮሐንስን፡ፈር፡በመከተል፡አግዐዚ፡በማለት፡ከትግራይ፡ዱዳ፡ባላገር፡መልምለው፡እዬ፡ቀለቡ፡የፋሽስቱ፡አመፀኛ፡ከሃዲ፡ኤርትራዊ፡ዓረብ፡ለገሠ፡ዜንዝዊ፡አሥረሥ፡ጠባቂ፡ሆኖ፡ቀሪው፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡በማስራብ፡ያሰቃያሉ።ዐፄ፡ዮሐንስ፡፬ኛና፡የትግራ

ይ፡ወያኔዎች፡በአፍ፡እዬ፡ደለሉ፡በተግባር፡ግን፡ኢትዮጵያን፡በስሟ፡ከመጠቀም፡በስተቀር፡እንደ፡እምዬ፡ዳግማዊ፡ምኒልክ፡አርቀው፡በማሰብና፡ሕዝብን፡በማስተባበር፡ለመላ፡ኢትዮጵያውያን፡ዜጎች፡ቆመው፡ለማልማት፡የተዘጋጁ፡አልነበሩም/አይደሉም።

ያለንበት፡ግዜ፡ያለ፡ማስረጃና፡ዋቢ፡ሳይጠቀስ፡ቢጻፍ፡አመኔታና፡እንደ፡ፋሽስቱ፡አረመኔ፡ለገሡ፡ዜናዊ፡አሥረሥ፡የታወቀላቸው፡ዋሾዎች፡እንዳንባል፡የጐንደር፡ገበሬ፡የደረሰበትን፡በደል፡ለዐፄ፡ዮሐንስ፡አቤቱታ፡አቅርቦ፡የሰጡትን፡መልስና፡በዬ፡ግዜው፡ከጐንደር፣ከጐጃምና፡ወሎ፡ሕዝብ፡የተሰሙትን፡እንጉርጉሮዎች፡እናስታውሳችሁ፡-“.........፡በአጠቃላይ፡ከመጋቢት፡እስከ፡ኅዳር፡ዋዜማ፡ድረስ፡የበጌምድርና፡ስሜን፡ገበሬ፡ሚስቱ፡በማጀቷ፣ገበሬው፡በጓሮው፡አያዙበትም።አዛዡ፤ተሠሪው፡ሠራዊት፡ነው።ገበሬው፣ሚስቱና፡ልጆች፡የተሠሪው፡ሠራዊት፡እግር፡አጣቢ፣አልጋ፡አንጣፊ፣ለበቅሎና፡ፈረስ፡ገፈራ፡አቅራቢና፡ሣር፡አጫጆች፡ናቸው።ለገበሬውና፡ቤተ፡ሰቡ፡ብርቅ፡የሆኑትን፡ማር፣ቅቤና፡ሥጋ፡ሳያጓደል፡ለሠራዊቱ፡ማቅረብ፡ግዴታው፡ነበር።ተሠሪው፡ሠራዊት፡ያለ፡ሐሳብ፡ገበሬውን፡አስገድዶና፡አስጨንቆ፡የሚመገበው፡ሥጋ፣ማርና፡ቅቤ፡ሰውነቱን፡ከማደርጀቱም፡በላይ፡ፍትወተ፡ሥጋ፡ፍላጐቱን፡ከፍ፡ስለሚያደርገው፣የገበሬውን፡ሚስትና፡ሴት፡ልጆች፡እያስገደደ፡ይደፍራል።ይህን፡በተመለከተ፡አቶ፡ካሣ፡ገብረየስ፡በተባለ፡የበጌምድርና፡ስሜን፡ገበሬ፡የደረሰውን፡በደል፡ለአብነት፡ያህል፡መጥቀስ፡ይቻላል።

አቶ፡ካሣ፡ዕለታዊ፡ተግባሩን፡ለመከወን፡ከቤቱ፡ሲወጣ፡ተሠሪው፡የዐፄ፡ዮሐንስ፡ወታደር፡ሚስቱን፡ልድፈርሽ፡በማለቱ፣ሴትዮዋ፡በክብሯ፣በሃይማኖቷና፡በታማኝነቷ፡ፀንታ፡አሻፈረኝ፡አለችው።ወታደሩ፡ግን፡እንቢታዋን፡እንደ፡ንቀት፡ቆጥሮ፡አሳቻ፡ጊዜ፡እየጠበቀ፡በኃይል፡ለመድፈር፡የተደጋገመ፡ሙከራ፡አደረገ።የአቶ፡ካሣ፡ሚስት፡ባልጠበቀችው፡ሁኔታ፡በዚህ፡ወታደር፡እንዳትደፈር፡በመስጋትና፡የባሏንና፡የእርሷንም፡ክብር፡ለመጠበቅ፡በማሰቧ፤ባለቤቷ፡ወደ፡ሥራ፡ሲወጣ፡እግሩን፡ተከትላ፡ቤቷን፡ጥላ፡እየወጣች፡ቀኑን፡ከባሏ፡ዘመዶች፡ቤት፡ማሳለፍ፡መረጠች።

አቶ፡ካሣ፡ሥራ፡ውሎ፡ሲመለስ፡የእግር፡ውኃ፡ቀርቦለት፡ታጥቦ፡እንዳበቃ፡በቅድሚያ፡መቆያ፡ቀጥሎም፡እራት፡ይሰጠው፡የነበረው፡የተገላቢጦሽ፡ሆኖ፡በማየቱ፡“ቀን፡ቀን፡የት፡እዬ፡ዋልሽ፡ነው፡እኔ፡ሥራ፡ውዬ፡ስገባ፡የምበላው፡በማቅረብ፡ፈንታ፡ድስትና፡ምጎጎ፡የምትጥጅው?”።በማለት፡ጠዬቃት።ሚስቱም፡ያለ፡መርበትበት፡“ቀንማ፡እንዴት፡ብዬ፡ወጥ፡ልሥራ፣እንጀራ፡ልጋግር?።አንተ፡እያረስክ፣እዬ፡ፈጨሁና፡እዬ፡ጋገርኩ፡የምንቀልበው፡ተሠሪው፡ሰውዬ፡ካልደፈርኩሽ፡እያለ፡አስቸገረኝ።እኔም፡የሀብታችንና፡የጉልበታችን፡ተጠቃሚ፡መሆን፡በዝቶብን፡እያንገሸገሸኝ፡ባለበት፡ወቅት፡ጭኔን፡አንስቼ፡ከምጋደም፡ለሁለታችንም፡ውርደትና፡ከእርሱ፡ጋር፡የሞት፡ሞት፡መስሎ፡ስለ፡ታየኝ፡ሥራዬን፡ትቸ፡ከዘመዶችህ፡ቤት፡ቀኑን፡ማሳለፍ፡መረጥኩ።ወጥ፡መሥራቱና፡እንጀራ፡መጋገሩን፡አንተ፡ስትገባ፡ማከናወን፡የመረጥኩት፡ከመደፈር፡የሚያድነኝ፡ሆኖ፡ስላገኘሁት፡ነው”።በማለት፡ምሬቷን፡ነገረችው።

ተሠሪው፡ወታደር፡ሚስቱን፡ለመድፈር፡ያደረገው፡ሙከራ፡ያበሳጨውና፡ያናደደው፡አቶ፡ካሣ፡ሳይውል፡ሳያድር፡ለንጉሡ፡አቤቱታ፡ማሰማት፡እንዳለበት፡ወሰነ።በውሳኔውም፡መሠረት፡በጧቱ፡ወደ፡ንጉሡ፡ችሎት፡ደብረ፡ታቦር፡ኀሩይ፡ጊዮርጊስ፡አቀና።ኀሩይ፡ጊዮርጊስ፡እንደ፡ደረሰም፡ጮኸት፡ማሰሚያው፡ቦታ፡ቆሞ፡“ጌታዬ!፡አቤት!፡አቤት!፡የሚለውን፡ጩኸት፡አሰማ።በደንቡ፡መሠረትም፡የንጉሡ፡አጋፋሪዎች፡ወደ፡ችሎቱ፡አቀረቡት።

“አቤት፡ጌታዬ!፡እግዚአብሔር፡ያሳይዎ፡ክርስቶስ፡ያመልክትዎ፡............እኔ፡እያረስኩ፣ሚስቴ፡እዬ፡ፈጨች፣እዬ፡ጋገረችና፡እግሩን፡እያ፡ጠበች፡የምንቀልበው፡የንጉሡ፡ወታደር፣እኔ፡ወደ፡ሥራ፡ስሄድ፡ሚስቴን፡ካልደፈርኩሽ፡እያለ፡አስቸግሯታል።ንጉሥ፡ሆይ፣እርሱ፡ተነሥቶ፡ሌላ፡ጨዋ፡ሰው፡ይመደብልኝ”።ብሎ፡በደሉን፡አሰማ።ዐፄ፡ዮሐንስ፡የአቶ፡ካሣን፡አቤቱታ፡ካዳመጡ፡በኋላ፣ጉዳዩን፡በዐቃቤ፡ሰዓት፡ለማየት፡ካሣ፡እንዲወጣ፡ተደረገ።በንጉሡ፡ሰብሳቢነት፡የመኳንንቶች፡ጉባዔ፡በአቶ፡ካሣ፡አቤቱታ፡ላይ፡ተወያይቶ፡የደረሰበት፡ውሳኔ፡በንጉሡ፡አንደበት፡ለአቤት፡ባዩ፡እንዲነገር፡ስምምነት፡ላይ፡በመደረሱ፡አቶ፡ካሣ፡እንዲገባ፡ተጠራ።ዐፄ፡ዮሐንስም፡“አብዳው፡እንጂ!፡ምፅሪ፡ከትግራይ፡ጭኖ፡ሊመጣ፡ነው?።ብለው፡ነገሩት።..........፡ይህ፡ወሳኔ፡የካሣን፡ብቻ፡ሣይሆን፡የመላውን፡የበጌምድርንና፡ስሜንን፡

ሕዝብ፡ክብር፡ያዋረደ፡ነው።ካሣ፡ግን፡የንጉሡን፡ውሳኔ፡አሜን፡ብሎ፡ባለ፡መቀበል፡የዚያኑ፡ዕለት፡ማታ፡ገስግሶ፡የተሠሪውን፡ወታደር፡አንገት፡በጐራዴ፡ቀንጥሶ፡“ዱር፡ቤቴ”፡ብሎ፡ተሰደደ።

ዐፄ፡ዮሐንስ፡የወታደራቸው፡አንገት፡ተቆርጦ፡መሞቱን፡እንደ፡ሰሙ፡የካሣና፡የሰባት፡ትውልዱ፡ንብረት፡እንዲወረስ፡አዘዙ።ትዕዛዙም፡ተግባራዊ፡ሆነ።የአቶ፡ካሣና፡የዘመዶቹ፡ንብረት፡መወረስና፡መዘረፍ፡ሰበብ፡ሆኖ፡የአያሌ፡ዜጎች፡ንብረት፡ተዘረፈ።ቀደም፡ሲል፡ጀምሮ፡ተሠሪ፡ሠራዊታቸው፡በሕዝቡ፡ላይ፡ካደረሰው፡ግፍ፡ጋር፡ተደምሮ፡ለካሣ፡አቤቱታ፡የተሰጠው፡ውሳኔ፡“እንግዳ፡አብሮ፡ይበላል፡እንጂ፡የአስተናጋጅን፡ሚስት፡አይካፈልም”።እና፤“በአባት፡ርስትና፡በሚስት፡የለም፡ዋዛ”።በሚል፡ባሕላዊ፡ቀመሮች፡ፅኑ፡እምነት፡ያለው፡የበጌምድርና፡ስሜንን፡ሕዝብ፡በንጉሡ፡አገዛዝ፡ላይ፡የነበረውን፡ቅራኔ፡አባባሰው።

ፅኑ፡ሃይማኖታዊ፡እምነት፡እንደ፡ነበራቸው፡የሚነገርላቸው፡ዐፄ፡ዮሐንስ፡ሠራዊታቸው፡የገበሬውን፡የሕግ፡ሚስት፡ከክንዱ፡ፈልቅቆ፤ልጃገረድ፡ልጆቹን፡አስገድዶ፡ለፈጸመው፡የዝሙት፡ወንጀል፡ፍትሕ፡እንዲሰጡ፡ለቀረበላቸው፡አቤቱታ፡የሰጡት፡ውሳኔ፡ሃይማኖታዊም፡ሕጋውም፡አልነበረም።ይህ፡የዐፄ፡ዮሐንስ፡ውሳኔ፡በበጌምድርና፡ስሜን፡ሕዝብ፡በጥላቻና፡በመናናቅ፡ስሜት፡እንዲተያዩ፡አድርጓል።በመሆኑም፡የበጌምድርና፡ስሜን፡አባቶች፡ተበልቶ፤ተጠጥቶ፡ሲያበቃ፡በሚደረግ፡የማሳረጊያ፡የጸሎትና፡የምረቃ፡ሥነ-ሥርዓት፡ላይ፡“አገሬ!፡ከትግሬ፡ተሠሪ፤ከቀዳዳ፡ሱሪ፡ያድንህ!”።በማለት፡ይመረቅ፡እንደ፡ነበር፡ዛሬም፡እንደሚመረቅበት፡ይታወቃል።ውሳኔው፡“ትግሬ፡አስተዳደር፡አይችልም”።ለሚል፡የተዛባ፡አባባል፡መነሻ፡ሆኗል።ከዚህም፡የተነሳ፡ዐፄ፡ዮሐንስ፡በ፲፰፻፹፩፡ዓመተ፡ምሕረት፡ወደ፡መተማ፡ዘምተው፡ከደርቡሾች፡ጋር፡ባደረጉት፡ጦርነት፡የበጌምድር፡ሕዝብ፡ተሳትፎ፡የጠበቁትን፡ያህል፡እንዳልነበር፡አባቶች፡ይናገራሉ።

አቶ፡ካሣ፡ገብረየስ፡ዐፄ፡ዮሐንስ፡መተማ፡ላይ፡ሲሞቱና፡አልጋቸው፡በምኒልክ፡ሲያዝ፡ወደ፡ሰላማዊ፡ኑሮው፡ተመልሶ፡ምኒልክ፡“እውነተኛው፡የበጌምድር፡ጀግና፡አንተ፡ነህ”።በማለት፡የፍታውራሪነት፡ማዕረግ፡የሰጡት፡መሆኑ፡ታውቋል።ካሣም፡ጀግንነቱን፡በሚስቱ፡ነጣቂ፡ላይ፡ብቻ፡ሳይሆን፡በአገር፡ነጣቂ፡ላይም፡በማስመስከር፡በ፲፰፻፹፰፡ዓመተ፡ምሕረት፡ዐድዋ፡ላይ፡ጣሊያን፡ጋር፡በተደረገው፡ጦርነት፡ሙያ፡ሠርቶ፡እንደ፡ተሰዋ፡አቶ፡እርቅዬ፡አድማሱ፡ከአባታቸው፡የሰሙትን፡ነግረውኛል”።*፲፪፡ገጽ፡'፫፻፲፩-፫፤ሥልጣን፡ተሻሚ፡ትግሬዎችና፡የኢትዮጵያ፡አንድነት።በተክሌ፡የሻው፤፪ሺ፡ዓመተ፡ምሕረት።

እንግዴህ፡መጻሕፍትን፡አገላብጠን፡የማንኛውንም፡ደራሲ፡አመለካከት፡ስንመለከት፡የዐፄ፡ዮሐንስን፡ለሥልጣን፡ጥመኝነት፡አነሣሥ፡በጣም፡ጎልቶ፡እናነባለን።ኃያላንና፡ታዋቂ፡የኢትዮጵያ፡ነገሥታትን፡ስም፡እዬ፡ጠቀሱ፡የነከሌ፡ልጅ፡ነኝ፤ወገን፡ነኝ፡በማለት፡ለእንግሊዞችም፡ለፈንሣይዎች፡በጻፏቸው፡ደብዳቤዎቻቸው፡አረጋግጠውልናል።

በእርሳቸው፡ዘመን፡ስላደርሱባቸው፡ሰቆቃ፡የተነገሩ፡እንጉጉሮዎች፡-በ፲፰፻፹፡ዓ.ም.ጥር፡፲፡ቀን፡ደርቡሾች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡አቃጥለው፡ቀሳውስቱንና፡መነኮሳቱን፡ሁሉ፡አረዷቸው።ገሚሱንም፡በምርኮ፡ስም፡እዬ፡ያዙት፡ሲሄዱ፡ከምርኮኛው፡አንዱ፡ከዚህ፡ቀጥሎ፡ያለውን፡ገጠመ፡-

፩- “ተከተልከኝ፡ብዬ፡ዞሬ፡ዞሬ፡ሳይ፤
ወይ፡ጥጋብ፡ወይ፡ኩራት፡ጎንደር፡ቀረህ፡ወይ!?፤
ወገራ፡አሳላፊ፡ደቢያ፡እንጀራ፡ጣይ፤
ተበላህ፡ጎንደሬ፡አትነሣም፡ወይ!።”

፪- “ጃንሆይ፡ልንገርዎት፡ትንሽ፡አማርኛ፤
ላሙን፡በሬውንም፡ወሰደው፡ገንቦኛ፤
ለምን፡ሆድ፡አይዘርፉም፡አርፈን፡እንድንተኛ”።

፫- ከጐጃም፡ሴት፡- “ዘንድሮ፡ንጉሡ፡ደህና፡ቢመለሱ፤
ምንኛ፡ጐልድፏል፡ጐጃሜ፡ምላሱ።

፬- ከወሎዎች፡- “የዮሐንስ፡በቅሎ፡ብረኪ፡ብረኪ፤
በመተማ፡በኩል፡መጣልሽ፡ማራኪ።

፫- ክርስቲያን፡ነኝ።“የክርስቲያንን፡ደም፡ለመበቀል፡ነው”።ብለው፡ከደርቡሽ፡ጋራ፡ጦርነት፡ያወጁት፡ንጉሥ፡ጐጃምን፡የሠሩበት፡ግፍ፡-“ያዔ፡ዮሐንስ፡ወታደር፡በጉዛምንና፡ማቻከል፡የተገኘውን፡የቤተ፡ክርስቲያን፡ሣንቃ፡እዬ፡ነቀለ፡በጭምት፡አፋፍ፡የጥይት፡ማብረጃ፡ለማድረግ፡ተራውን፡(ተርታውን)፡አቁሞ፡ማገሩን፡እዬ፡ነቀለ፡ማንደድ፣ታቦቱን፡ከመንበሩ፡እያወጣ፡በዬ፡ሜዳው፡በጣለው፡ጊዜ፡ጳጳሱ፡አቡነ፡ሉቃስ፡በንዴት፡“ደርቡሽን፡አጠፋለሁ፡ብዬ፡መጣሁ፡ያልከው፡በጐጃም፡አንተ፡ደርቡሽ፡ሆንክ”።ብለው፡ዐፄ፡ዮሐንስን፡መቆጣታቸውን፤..................፡ተናደው፡ብዙ፡ጭፍራ፡ሰደው፡ጐጃምን፡ከፉኛ፡ማዘረፋቸውን፡.............፡በዚሁ፡ወረራ፡ልብሷን፡የተገፈፈችና፡ከብቶቿ፡የተነዱባት፡አንዲት፡የጐጃም፡ሴት፡-

“በላይኛው፡ጌታ፡በባልንጀራዎ፣
በቅዱስ፡ሚካኤል፡በጋሻ፡ጃግሬዎ፣
በጽላተ፡ሙሴ፡በነጭ፡አበዛዎ፣
ጎጃምን፡ይማሩት፡ፈሪም፡አንልዎ”። ዐፄ፡ዮሐንስ፤በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ፡፲፱፻፹፪፤፫፻፴-፫።

፬- በግዳጅ፡ክርስቲያን፡መሆኑ፡ያሳዘነው፡የወሎ፡እስላም፡-

“ታላቅ፡ታናሽ፡በላን፡ከርካ፡አደባባይ፣
ክርስቲያን፡ሆይ!፡አለልብ፡ሥጋ፡ይጣፍጣል፡ወይ?።

፭- ዐፄ፡ዮሐንስ፡መተማ፡በጦርነቱ፡ውስጥ፡መሞታቸው፡ሲሰማ፡ንጉሥ፡ተክለ፡ሃይማኖት፡አኅበር፡ያስተክሉና፡እዚያ፡ውስጥ፡የንጉሥ፡ነገሥቱን፡ምሥል፡አስቀምጠው፡የጎጃምን፡ሕዝብ፡ክተት፡ብለው፡እንዲያለቅስ፡ያዝዙታል።ከዚያ፡አንድ፡አስለቃሽ፡ትመጣና፡_

“ሲገዙ፡እንዳልኖሩ፡እንዳልበሉ፡ሁላ፣
ለተባይ፡ሰጥተውን፡ዳርገውን፡ለተኩላ፣
ወጥተው፡ሲቀመጡ፡ንጉሡ፡ጅበላ፣
በጃችን፡ሳይጠጣ፡በጃችን፡ሳይበላ፣
ደም፡መላሽ፡ሆነን፡መሀመድ፡አብደላ፣
ዘሩን፡ይባርክለት፡የሚያምንበት፡አላ”።

ስትል፡ንጉሡ፡ተቆጥተው፡እንድትያዝ፡ያደርጉና፡ልቅሶው፡እንዲቀጥል፡ያዝዛሉ።ከዚያ፡ሁለተኛይቱ፡አስለቃሽ፡ትነሣና፡-

“ደህና፡ተሰላድቷል፡ተጠርጓል፡መንገዱ፣
ዐፄ፡በሄዱበት፡ንጉሡም፡ይሂዱ”።

ስትል፡ለልቅሶ፡የከተተው፡ሕዝብ፡በማልቀስ፡ፈንታ፡በሣቅ፡ያወካል።ያን፡ጊዜ፡ንጉሡ፡የሚያደርጉትን፡አጥተው፡“የተያዘችውን፡አስለቃሽ፡ልቀቁ፡“ብለው፡ልቅሶውን፡ፈትተው፡ተነሡ፡ይባላል። *ሌላ፡ሌላም፡መጨመር፡ይቻል፡ነበረና፡ለግዜው፡በዚህ፡እንግታው።

*ገጽ፡፫፻፸፩፡የልም፡እዣት፤በሊቀ፡ምሁር፡ሐዲስ፡ዓለማዬሁ።፲፱፻፹፡ዓ.ም.

## ራስ፡አሉላ፡እንግዳ፡-

“ራስ፡አሉላ፡በኢትዮጵያ፡ታሪክ፡ውስጥ፡አኩሪና፡መልካም፡ታሪክ፡ካላቸው፡ሰዎች፡መካከል፡አንዱና፡የመጀመሪያው፡ረድፍ፡የሚሰለፉ፡ዕውቅ፡የጦር፡ጀኔራል፡አርቆ፡አሳቢ፣ላእከ፡መንግሥት፣ቆራጥ፣ብልኅ፡ወታደርና፡የጦር፡መሪ፡ናቸው”።የራስ፡አሉላ፡ታሪክ፡ውስጥ፡የጎላ፡ቦታ፡እንድይዝ፡ካደረጉት፡ተግባሮቻቸው፡አንዱና፡ዋናው፡የባሕረ፡ነጋሽ፡ገዥ፡በነበሩበት፡(በ፲፰፻፹፰፡ዓ.ም.)፡ወቅት፡ከምፅዋ፡ተንቀሳቅሶ፡መላ፡ኢትዮጵያን፡በቅኝ፡ግዛት፡ቀንበር፡ሥር፡ለማዋል፡የተሰለፈውን፡የጣሊያን፡ጦር፡ሠራዊት፡ዶጋሊ፡ላይ፡ገጥመው፡ድል፡የነሱበት፡ነው።ይህ፡ድል፡ወታደራዊ፡ብቻ፡ሳይሆን፡ላእከ፡መንግሥታዊ፡ጭምር፡ነበር።ድሉ፡በአፍሪካ፡የቅኝ፡ግዛት፡ታሪክ፡ውስጥ፡በዘማናዊ፡መንገድ፡የተደራጀ፣የሠለጠነና፡የታወቀ፡አውሮፓዊ፡ኃይል፡በጥቁር፡ኃይል፡መቋቋም፡ብቻ፡ሳይሆን፡ድል፡ማድረግም፡እንደ፡እሚቻል፡በቅኝ፡ግዛት፡ሥር፡ለሚማቅቁ፡ሕዝቦች፡ለመጀመሪያ፡ጊዜ፡ትምህርት፡የሰጠ፡ነበር።ይሁን፡እንጂ፣ይህ

ገጽ፡፰-፲፩፤

ን፡በአፍሪካ፡ፀረ፡ቅኝ፡አገዛዝ፡ተጋድሎ፡ውስጥ፡ጉልህና፡ፈር፡ቀዳጅ፡ሚና፡የተጫወተውን፤በተለይም፡በኢትዮጵያ፡ነፃነትና፡አገራዊ፡ታሪክ፡ውስጥ፡የለየ፡ቦታ፡ያለው፡የዶጋሊን፡ድል፡ባለቤት፡ሹሞ፤ሸልሞ፡ለተጨማሪ፡ታሪካዊ፡ኃላፊነት፡እንዲዘጋጁ፡ከማድረግ፡ይልቅ፣ዐፄ፡ዮሓንስ፡የራስ፡አሉላን፡አንገት፡የሚያስደፋ፤በአገሪቱ፡ነፃነት፡ላይ፡አደጋን፡የሚጋብዝና፡ድል፡የተነሳው፡የጣሊያን፡ጦር፡የሚያንሰራራበትን፡ተግባር፡ፈጸሙ።“ራስ፡አሉላ፡ዶጋሊ፡ከጣሊያን፡ጋር፡ያደረጉት፡ጦርነት፡ከእኔ፡ዕውቅና፡ውጪ፡ነው”፡በሚል፡ምክንያት፡ከባሕረ፡ነጋሽ፡ግዛታቸውና፡ከጦር፡አዛዥነታቸው፡አጋዟቸው።**ገጽ፡፫፻፳፬፡ሥልጣን፡ተሻሚ፡ትግሬዎችና፡የኢትዮጵያድነት፤፪ሺ፡ዓ.ም.በተክሌ፡የሻው።*ገጽ፡፫፻፺፤ዐፄ፡ዮሐንስ፤በተክለ፡ጻድቅ፡መኩሪያ፣፲፱፻፹፪።



ራስ፡አሉላ፡እንግዳ።

ለኢትዮጵያ፡አንድነትና፡የባሕር፡ወደቧን፡አስከባሪ፡የነበሩት፡አገር፡ወዳዱ፤ጀግናው፣ብልኁ፣ደፋሩና፡አርቆ፡አሣቢው፡ኢትዮጵያዊ፡ራስ፡አሉላ፡እንግዳ፡ነበሩ።

ዐፄ፡ተክለ፡ጊዮርጊስን፡በመማረካቸው፡-
“ንጉሥ፡ማራኪ፡ከነ፡ዘውዱ፣
የበዝብዝ፡አሽከር፡አሉላ፡ወንዱ፤
ከነፋስ፡የፈጠነ፣
በወንድነቱ፡የተማመነ፤
ክንዱ፡ብርቱ፡እንዳንበሳ፣
በጠላት፡ሠፈር፡የሚያገሳ”።*ሀ ተብሎ፡ተገጥሞላቸዋል።

በዶጋልሊው፡ጦርነት፡የራስ፡አሉላ፡የጉብዝና፡ዝና፡በመላው፡ኢትዮጵያ፡ተሠራጭቷል።በኢጣሊያኖችም፡በኩል፡ከማናቸውም፡የዐፄ፡ዮሐንስ፡መኰንን፡የበለጡ፡የታወቁና፡በየመጽሐፉ፡የሚታወሱ፡ናቸው።ከዶጋሊ፡ጦርነት፡ወዲህ፡በየጊዜው፡እንደዚህ፡እየተባለ፡ተግጥሞላቸዋል፡-

፩- መብቱን፡ዮሐንስ፡ላሉላ፡ቢሰጠው፣
እንደ፡ቀትር፡እሳት፡ቱርክን፡ገላመጠው፣
ጣልያንም፡ወደቀ፡እያንቀጠቀጠው፣
አጭዶና፡ከምሮ፡እንደ፡ገብስ፡አሰጣው።
፪- አባ፡ነጋ፡አሉላ፡ካሥመራ፡ቢነሣ፤
እንዳንበሣ፡ሆኖ፡እሳት፡እያገሣ፣
የችግር፡ምስጋና፡ባይወሳ፣
ቢቸግረው፡ጣልያን፡አለ፡ፎርሳ፡ፎርሳ፤
፫- ጣሊያን፡በሀገርህ፡አልሰማህም፡ወሬ፣
የበዝብዝ፡አሽከሮች፡እነ፡ሞት፡አይፈሬ፣
ዘለው፡ጉብ፡ይላሉ፡እንደ፡ጐፈር፡ዐውሬ፤
፬- አባ፡ነጋ፡አሉላ፡የደጋ፡ላይ፡ኮሶ፣
በጥላው፡ያደክማል፡እንኳንስ፡ተቀምሶ፤
፭- ጣሊያን፡ሰሐጢ፡ላይ፡እግሩን፡ቢዘረጋ፣
በብረት፡ምጣዱ፡በሰሐጢ፡አደጋ፣
አንገርግቦ፡ቆላው፡አሉላ፡አባ፡ነጋ፤
፮- ተው፡ተመከር፡ጣሊያን፡ይሻላል፡ምክር፣
ሰሐጢ፡ላይ፡ሆነህ፡መሬት፡ብትቆፍር፣
ኋላ፡ይሆንሃል፡ላንተው፡መቃብር፣
ይቺ፡አገር፡ኢትዮጵያ፡የበዝብዝ፡አገር፣

ምንም:አትቃጣ:አንዳራስ:ነብር።

ይሁን:እንጂ፣በዶጋሊ:የራስ:አሉላ:አሸናፊነት:ያለ:ፈቃዴ:ተዋጋህ:በማለት:በንጉሥ:ነገሥቱ:ዘንድ:ቅሬታ:ሲያሳድር፣በሌላ:በኩል:በንጉሠ:ነገሥቱ:ዙሪያ:የነበሩ:መሳፍንትና:የንጉሠ:ነገሥቱ:ቤተ:ሰቦች:ሳይቀሩ፣ባንድ:ወገን:አሉላ:ከተራ:ቤተ:ሰብ:የተወለዱ:መሆናቸውን:በመጥቀስ፤በሌላ:በኩል:ጠላትን:በማሸነፍ:ዝናቸው:እዬ:ገነነ:በሔደ:መጠን:ለወደ:ፊቱ:አስፈሪ:ሊሆን:ይችላል:በማለት:በንጉሡ:ዘንድ:ጥላቻና:ጥርጣሬ:እንዲያድር:ያደርጉ:ነበር:ይባላል"።*ለ *ሀ-ገጽ:፳፱።*ለ-ገጽ:፫፻፺-፺፩፤ዐፄ:ዮሐንስ:በተክለ:ጻድቅ:መኩሪያ።፲፱፻፹፪።

በመጨረሻም:ራስ:አሉላ:ከደጃዝማች:ሐጎስ:ጋራ:በግዛት:ተጣልተው:ሲፋለሙ:ደጃዝማች:ሐጎስ:ተሸንፈው:ሲሞቱ፣ራስ:አሉላ:በደረሰባቸው:የመቁሰል:አደጋ:ሰበብ:ዓርፈዋል።የጀግና:እናት:በድባብ:ትሂድ።የራስ:አሉላን:ነፍስ:ይማር።ኢትዮጵያም:ዛሬ:እንደሳቸው፣ዐፄ:ምኒልክና:ዐፄ:ቴዎድሮስ:የመሳሰሉ:ጀግናዎቿን:በመናፈቅ:ላይ:ስለ:ሆነች:ከወንድ:ልጆቿ:አንዱ:ብቅ:እንደሚል:አንጠረጠርም።

የዘመናችንን:ሁኔታ:ስንመለከትም:በአፍቃሬ:ዮሐንስ:የትግራይ:ወያኔዎች:ለሥልጣንና:ዘረፋ:እንጂ፣ኢትዮጵያውያንን:አስተባብረው:መሥራት:አለ:መፈላጋቸውን:ለሃያ:አመታት:እያዬናቸው:ነው።ስለዚህ፣ፋሽስቱ:አመፀኛ:ኤርትራዊው:ዓረብ:ለገሠ:ዜናዊ:አሥረሥ:ክከሃዲው:አያቱ:ደጃዝማች:አሥረሥ:በወረሰው:ተንኮል:ሕዝብና:ሕዝብን:በማበጣበጥ:አከፋፍሎ:አገር:ለማጥፋት:ያቀደውን:ቀጥሎበታል።

ከሀገረ:እግዚአብሔር:ወሕዝበ:ኢትዮጵያ:አስተምህሮ:ለኩሉ:ዓለም:ያታላላቅ:ታላቅ:ሕዝባዊ:ስብሰባ:ጥሪ።በመምህር:ሐጎስ:ዓለማዬሁ።ገጽ:፳፯፤



67

Two consultative organs will be placed at the central government's disposal. The first is the Council of Government, presided over by the Viceroy or in his absence by the Vice Governor-General and composed of the empire's highest officials. The second is the Board of Consultors, composed of prominent white colonists and six native chieftains. All members of the Board of Consultors will be appointed by the Viceroy.

Regional Governments

The five regional Governments will be:

The Government of Eritrea, with its capital at Asmara, comprising the old colony of Eritrea plus Tigre and Danakil Provinces of Ethiopia as far south as French Somaliland.

The Government of Amhara, with its capital at Gondar, comprising all Amharic populations of the high plateau from the region of Lake Tana as far south as and including Shoa.

The Government of Galla and Sidamo, with its capital at Jimma, comprising all the territories of Southwestern Ethiopia inhabited by the Gallas and Sidamos from the great lakes to the Sudan frontier.

The Government of Harar, with its capital at Harar, comprising all the lands inhabited by the Moslem populations of Harar, Arussi and Bale Provinces.

The Government of Somaliland, with its capital at Mogadiscio, comprising the whole of the old Italian Somaliland, plus Ogadan Province of Ethiopia.

The regional Governments are to be headed by and represented by Governors, each of whom will have at his service a secretary general in charge of civil affairs and a commander of troops in charge of military affairs. Technical officers will be in charge of civil and political services. Each Government will be divided into districts known as Commissariats, which in turn will be divided into smaller districts known as Residencies and Vice Residencies.

The most important inhabited centers, including the capitals of the five regional Governments, will be raised to the rank of municipalities.

Some Regional Autonomy

The five regional Governments will be subordinate to the central government at Addis Ababa for

Today's communiqué emphasizes that the empire has been organized in such a way as to respect the interests and traditions of native populations. It points out that the empire has been divided into territories homogeneous from ethnical, geographical and historical viewpoints. Each great racial stock in the empire is to have its own territory and government.

The rights of the Moslem population are fully guaranteed and protected. Throughout the empire they are to be allowed to reopen their places of worship, religious insti-

The Ethiopian Coptic Christian Church is also fully guaranteed and protected. Agreements are to be reached with the clergy to provide for the greatest development of religion in the Christian territories of the empire and of the cultural and other ties that unite the Ethiopian church to the Egyptian Coptic Church.

The Viceroy must ask the opinion of the Board of Consultors on all questions affecting the life of the native populations of the empire. As the principal representatives of the native population are to have places reserved for them on this board, they will collaborate directly in the government of the empire.



ITALY DIVIDES CONQUERED ETHIOPIA

With Eritrea and Italian Somaliland included and enlarged five governments have been set up. Their boundaries are shown approximately and the capitals are underlined. Addis Ababa, with some surrounding territory, will be kept as a separate entity, the seat of the central authority.

ሥዕል አሥራ ስድስት

ፋሽስት ጣሊያንና ወያኔ አንድ ናቸው። ወያኔ ምንም እንኳን በአማርኛ ቋንቋ ክልል ይበለው እንጂ የፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በጎሳ የሸንሸነበትን ካርታ በቀጥታ በሥራ አውሎታል። ይህን የከፋፍለህ ግዛ ሥይጣናዊ ካርታም በሞሶሎኒ ትዕዛዝ ተቀርጾ የተዘጋጀ ነበር። በዕኩይ ሥራው [በአውሮጳውያን አጋንንት ዴሞክራሲ] ስም ወያኔ በሥራ ላይ አውሎት ያለ ነው። ይህም ካርታ እ. አ. አ. ሰኔ 2 ቀን 1936 ዓ. ም. ለአስረጅነት በኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣ የወጣ ነው።



የእናት:ሆድ:ዝንጉርጉር:እንዲሉ፣ትግራይ:መምህር:ሐጎስ:ዓለማዬሁን:የመሳሰሉ:የተወለዱባት:ኢትዮጵያዊት:አገር:ነበረች/ናት።



ጎጠኛው፡ኤርትራዊ፡ዓረብ፡አገር፡ሻጭና፡በረሃ ብ፡ነጋዴው፡ለገሡ፡ዜናዊ፡አሥረሥ፡ወንጀለኛ፡ስለ፡ሆነ፡ ማንኛውም፡ሕዝብ፡ሊያወግዘው፡ይገባል።በአንድ፡ዘር፡ ላይ፡አተኩሮ፡ሊሻሻሉ፡የሚገባቸውን፡በማርገብ፡ፈንታ፡ ወደ፡ዘመነ፡መሳፍንቱ፡ዘመን፡መልሶ፡ሊያበጣብጠን፡ እዩ፡ሞከረ፡ነው።እነዚህ፡ከሃዲዎች፡ያልተጠሉ፡ማን፡ ይጠላልና፡ትግሬን፡አትወዱም፡እያሉ፡ሕዝብ፡የሚያሰቃ ዩ።የጠላነው፡ዘረኝነታቸውን፡ነው።ኢትዮጵያችንን፡ለ ውጭ፡ዜጋ፡ከመሸጥ፡ይልቅ፡ድርሻችንን፡ይዘን፡አብራን፡ እንሥራ፡እያልን፡ነው።

ሌላው፡የትግሬ፡ጎጠኛ፡የከሃዲው፡ደጃዝማች፡ገብረ፡ሥላሴ፡ልጅ፡ደጃዝማች፡ዘውዴ፡ገብረ፡ሥላሴም፡ምኒልክ፡ኤርትራን፡በ፭፡ሚሊዮን፡ሊሬ፤ሉግ፡ፈርናንዲ፡[ሶማሊያ]ን፡በ፫፡ሚሊዮን፡ሊሬ፡ እንደ፡ሸጡ፡ሊነግሩን፡ቃጥቷቸዋል።ደጃዝማች፡ገብረ፡ሥላሴ፡የሚባሉት፡ከትግሬ፡መሬት፡በ፭፡ ጠበንጃ፡ለኢጣሊያ፡የሸጡ፡ናቸው።*፮፤-ኢትዮ፡ላዮን፡ጎዋ፡ሰሌዳ፤ጌታቸው፡ኃረደው፤ጀርመኒ። .......The fact that he did not attempt to pursue his victory by moving to Eritrea, and the subsequent settlement of the Ethiopian-Italian border which followed the Mareb-Belesa-Muna line against the payment of five million lire by the Italians in May, 1902, have also led to the allegations which are often made that "Menelik literally sold a number of villages with all their tnhabitants."................"A similar attitude can be seen in the South in dealing with the Italians over the region of Lugh Fernandi where the Italians were advancing from Somaliland. An area of 50,000 square kilometers was ceded for three million lire by a treaty concluded on May 16, 1908." *፯፡፳፬፤ *፯፤ ERITREA:AND:ETHIOPIA:IN:THE: CONEX :OF:THE:RED:SEA:AND:AFRICA:BY:ZEWDE:GEBRE-SELLASSIE:March1976.

በኢትዮጵያውያን፡የተነገሩ፡ስለ፡ምኖች፤-

፩- አገር፡ተላላ፡ነው፣
ወንዝ፡ተላላ፡ነው፣ይጓዛል፡እንደ፡ሰው፣
በዩ፡በሩ፡ቁሞ፡ጀግና፡ካልመለሰው።

፪- ቆረጡት፡ያንን፡ዛፍ፡እነ፡ጣም፡አያውቁ፣
ምን፡ያፈራ፡ይሆን፡ብለው፡ሳይጠይቁ፤

፫- አርሲን፡ምን፡ነካው፡በስሜት፡ተነዳ፣
እህል፡ሳይቸግረው፡ገባ፡የሥጋ፡እዳ፤
በሐረርጌ፡በኩል፡ጨኸት፡በርክቷል፣
የሌላውን፡እንጃ፡አማራስ፡ተፈቷል፤

፬- የወያኔ፡ሠራዊት፡የከተት፡ዓይነት፡የገበሬ፡ሠራዊት፡መሆኑ፣ህልውናውም፡በዘረፋ፡ላይ፡መመ ሥረቱና፡ይህ፡ዓይነቱ፡ሠራዊትም፡በ፳፩ኛው፡ክፍለ፡ዘመን፡መግቢያ፡ላይ፡መኖሩ፤በዘረፋ፡የሚተዳደር፡ የገበሬ፡ሠራዊት ባሕል፡ከአገራችን፡ፈጽሞ፡ያልተ፡ወገደ፡መሆኑን፡የሚያሳይ፡ነው።የጐጃ ም፡ሕዝብ፡ ገጽ፡፲፩-፲፩፤

የወያኔ፡ሠራዊት፡በወረራና፡በዘረፋ፡የፈፀመበት፡ግፍ፣ዐፄ፡ዮሐንስ፡፬ኛ፡በሁለት፡ጊዜ፡ወረራ፡የፈፀ ሙትን፡ጭካኔ፡የተሞላበት፡ወረራ፡ስላስታወሰው፡-

ጦማችን፡ባይጠራ፡ጠሎታችን፡ቢያንስ፣
በልጅ፡ልጅ፡መጡብን፡ዐፄ፡ዮሐንስ፤

፭- ጐንደርም፡በበኩሉ፡የተፈጸመበትን፡ምዝበራ፡ለትግራይ፡ሕዝብ፡ለማመልከት፡-

ወያኔ፡ሃብታችንን፡ዘረፈው፡በሙሉ፤
መልሱ፡ያልን፡እለት፡አጣን፡እንዳትሉ፤

፮- እነዚህ፡በልገኞች፡እዩት፡ሲቀናጡ፣
ዐማራን፡አድኑት፡ብለው፡ትዕዛዝ፡ሰጡ፤

፯- የምትጠፋን፡አገር፡አውቃለሁኝ፡እኔ፣
በጭቃ፡ሹም፡አገር፡አምሳ፡ምስለኔ፤

፰- እጅ፡የሚያስቆረጥም፡ዶሮ፡ወጥ፡ካሻችሁ፣
ኢሣያስ፡አፈወቅ፡ከባረከላችሁ፣
ለመበለቱማ፡መለስ፡አለላችሁ፤

፱- አህያና፡ባንዳ፡ሁለቱ፡አንድ፡ናቸው፣
ጋማና፡ጅራት፡ነው፡የሚለያያቸው፤

፲- የሰማይ፡የምድር፡ገብቶብን፡ባንድ፡ዘር፣
ፍቺ፡ፍቺ፡ያላል፡የቅዳሴው፡መዝሙር፤

፲፩- አገሬ፡ተባብራ፡ካልረገጠች፡እርካብ፣
ነገራችን፡ሁሉ፡የእንቧይ፡ካብ፡የእንቧይ፡ካብ፤ በቀኝ፡ጌታ፡ዮፍታሔ፡ንጉሤ።፡

፲፪- ምድር፡ሁሉን፡ነገር፡ተሸክማ፡ስትኖር፣
የከበዳት፡የለም፡ከሰነፍ፡ሰው፡በቀር።
በዕውቀት፡ሥልጣኔ፡ግሎ፡ለመነሣት፤
ቆስቋሽ፡ይፈልጋል፡የሰው፡ልጅ፡እንደሣት። በከበደ፡ሚካኤል።

እግዚአብሔር፡ኢትዮጵያና፡ሕዝቧን፡አጠንክሮ፡ይባርክ።አሜን።

ዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ።

አስተያየት፡መስጠት፡ከፈለጉ፡- E-mail:- zienamarqos@yahoo.com